# Poverty action Network of civil society organizations in Ethiopia (PANE)

Capacity building assessment of CSOs on the adaptation of the new CSO law

**Funded by**

**DanChurchAid**

**December 2009**

# Addis Ababa, Ethiopia

# Introduction

Following the DCA agreement with PANE to implement a project on “Poverty assessment and climate Change Impact for Pro –poor Advocacy” there were four project component and one has been related with the Governance issues which include capacity building of CSOs particularly on the adaptation of the new CSO law.

For the achievement of this project rapid assessment has been held by a consultant and quantitative method was employed to reach all CSO categories i.e. Local, Ethiopian Resident and Foreign Charities and Societies.

The assessment was intensively held with the consultation of authorities particularly from the concerned bodies such as Ministry of Justice and the Agency for Charities and Societies.

PANE in its endeavor to meet the MDG/PASDEP facilitated various programs/projects to build the capcity of CSOs around the new legislation so as to help all stakeholders adopt the legislation and incorporate in their organization Vision, Mission and Goals.

# Objective

- The major objective of this specific project component is to make clear the difference between and among CSOs in the interpretation of the new CSO law particularly the articles that need further explanation.
- To build the capcity of CSO around the implementation process and adoption strategy with the new CSO law so as to strengthening their organization to effectively implement programs inline with their vision, mission and goals.

# Activities

Two major activities and other related sub activities have been performed in the context of this project component.

1. **Conduction Rapid assessment**

PANE has commissioned the work to the consultant specifying the detailed ToR with close follow up and supervision. The consultant with the overall coordination of PANE during the process of the rapid assessment has been dealt thoroughly with different CSOs and responsible Government bodies including the Ministry of Justice and the Agency for Charities and Societies. The research being conducted was at its standard using different methodologies.

The first draft of the research presented by the consultant was commented by PANE technical staff (Governance Unit), and some amendments have been included before the final draft to be presented in the workshop.

2. **Launching workshop for the presentation of findings of the assessment and further inputs**

The final draft of the assessment has been presented in the half – day workshop held at MN International Hotel dated December 18 2009.

Over 20 participants in the workshop were drawn from different CSOs of different categories (local, Ethiopian Resident and Foreign Charities). The findings were presented by the consultant including the research methods employed during data collection, analysis and interpretations.

Following the presentations, discussion on some points have been raised by the participants. The questions that have been traced are with in the assessment area and a lot of reflections were entertained during the session.

The Deputy Director General of the Agency has responded to all questions further to the assessment finding presented by the consultant. The major questions and answers and the overall achievements on the theme has been briefly explained in the **annexed minute**.

# Output

- Full-fledged document of the assessment conducted by the consultant was produced.
- Over 20 participants from different CSOs attended the workshop
- Minute that further elaborates questions and discussions particularly some key terms explained by the Deputy General of the Agency has been produced.
  (The minute is annexed)
- Participants with different questions and dialogues have been responded in accordance with the new law so as to help them adopt their development programs
- The workshop demonstrates further need to replicate the program not only at federal level but also at regional level as some of the reflections from the participants demands the necessity for replicating similar program.

# Way forward

It is possible to draw anticipated impact of the project on CSOs and responsible government bodies' particularly the Agency for Charities and Societies.

Thus the following could be identified as the possible impact to be accounted.

- CSOs with the built capcity in the interpretation of the new CSO law can change or adopt some of their strategic plan.
- CSOs will further develop different strategies on how to adopt the new CSO law provided that continuous similar project will be replicated both at federal and regional

level following the recommendations from the participants and the Deputy General of the Agency

- The Agency in its integrated work with CSO will have transparent relationship which could be significant during the implementation process.

# የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ አፈጻጸም እና አተረጓጐም ላይ የሲቪል ማህበራት ያላቸው ግንዛቤ ለማዳበር የተደረገ አውደ ጥናት ቃለ ጉባዔ

የስብሰባ ቦታ፡-    ኤም ኤን ኢንተርናሽናል ሆቴል

የስብሰባ ቀን/ጊዜ፡-  ታህሳስ 6 ቀን ከ2፡30- 6፡30

## 1. የመክፈቻ ንግግር

ወ/ሮ ዝናሽ ከፋለ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር፤ ፖአኔኢ የሲቪል ማህበራት ጥምረት እንደመሆኑ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ከመቋቋሙ በፊትም ጀምሮ ለሲቪል ማህበራት በረቂቅ አዋጁ ላይ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ከአራት ጊዜ በላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረቡን ጠቅሰዋል፡፡ በዚሁ ቀን የተደረገው አውደ ጥናትም ከ Dan Church Aid ጋር በመተባበር በአዋጁ አፈጻጸም ዙሪያ ያጋጠሙት ችግሮች ላይ ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ የጥናቱን ውጤት ለማዳበር አስተያየቶች እንዲቀርቡ በማድረግ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማዳበር የታለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አታክልቲ ግደይ ማብራሪያዎችን እንደሚሰጡ ገልጸዋል፡፡

## 2. ስለ ጥናቱ የተደረገው ማብራሪያ

አቶ ደበበ ኃ/ገብርኤል የጥናታቸውን ውጤት እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

የጥናቱ ዓላማ ኤጀንሲው ሥራ ከጀመረ በኂላ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ጥያቄዎች ምንድን ናቸው? የሚለውን ለመዳሰስ ነው፡፡

ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ከሲቪል ማህበረሰቡ ፍላጐት አንጻር መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው የሚለው ነበር፡፡ ሆኖም አሁን ያለንበት ሕጉ በጸደቀበት ጊዜ በመሆኑ የሲቪል ማህበረሰቡ በሕጉ መገዛት ስላለበት የሕጉን ማእቀፍ መወቅ እና ሕጉን መረዳት ግድ ይላል፡፡ ከዚህ መንፈስ በመነሳት ለውይይቱ ያግዛሉ በሚል የተወሰኑ ነጥቦች ተለይተዋል፡፡

በመንደርደሪያነት፤ በአዋጁ የተቀመጡት አደረጃጀቶችን ማለትም በጐ አድራጐት፣ ማህበራት፣ የበጐ አድራጐት ማህበር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበትን ነጥቦች በመጥቀስ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

I. ከዳግም ምዝገባ ጋር ተያይዞ የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን በሚመለከት ከሚነሱት ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1. በአምስት ክልሎች ስለመንቀሳቀስ በእዋጁ አንቀጽ 57 እና 69 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት በሚመለከት፡- ቀደም ሲል በነበረው አስተሳሰብ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ እንደ ክልሎች ቁጥር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ሲሆን ኤጀንሲው የፌደራል አወቃቀርን መሠረት ማድረግ አለበት በሚል ምክንያት እነዚህ ከተሞች እንደ አንድ ክልል ሊቆጠሩ እንደማይችሉ በስራ ሂደት ግልጽ አድርጓል፡፡
2. የአምስት ክልል ውክልናን በሚመለከት የህጉ መንፈስ የብሄር ተዋጽዖን ሳይሆን የክልል ነዋሪነትን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ መሆኑ በአሰራር እየጠራ መጥቷል፡፡
3. የአምስት ክልል ውክልናን በተመለከተ በአምስቱም ክልል ስራ ሳይጀመር ለወደፊት በአምስቱም ክልሎች መንቀሳቀስን ታሳቢ በማድረግ ተመዝግቦ ሥራ መጀመር እንደሚቻል በአሰራር ግልጽ ሆኗል፡፡
4. በአምስቱ ክልሎች የማይንቀሳቀሱ ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ስያሜን በመተው የመመዝገብ አዝማሚያ ታይቷል፡፡

II. “Advocacy” በአዋጁ ተከልክሏል የሚል አስተሳሰብን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 14 ላይ የበጐ አድራጐት ሥራ በሚል የተዘረዘሩትን ለማስፈጸም “advocacy”ን እንደ ስትራተጂ መጠቀም አይከለከልም በ“service delivery” ላይ የተሰማሩ ተቋማት የ“advocacy” ስራ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ምናልባት ይህ አመለካከት የመጣው “advocacy” ን ከሰብአዊ መብት ጥበቃ ጋር ስለሚያያዝ ይሆናል፡፡

III. ምዝገባን የሚያስከለክሉ ነጥቦች

መደራጀት መብት ነው ይህን መብት የሚገድቡ ነገሮች በህግ መሰጠት አለባቸው፡፡ የሚከለከለውም ሕጉን ጠቅሶ መሆን አለበት፡፡ ሕጉ objective standard ማውጣቱ በዘፈቀደ ይሰራ የነበረን የተዘበራረቀ አሰራር የሚያስቀር ስለሚሆን ጥሩ ጐን አለው፡፡

ለአዋጁ ፈቃድ ለማስከልከል በቂ ምክንያቶች ተብለው ለተዘረዘሩት አጠር ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

IV ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሌሎች ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ኤጀንሲው ሥራ ከጀመረ በኋላ በዳግም ምዝገባ ጊዜ የድርጅቱን ንብረት /ገንዘብ ዝርዝር እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር TIN No. ለኤጀንሰወ ማሳወቅ ለምዝገባ አንዱ መስፈርት ሆኗል፡፡ Withholding Tax እና የመሳሰሉት የግብር ግዴታዎች ስለመፈጸማቸው መረጃ እንዲቀርብ ኤጀንሲው መጠየቁም ሕጋዊ ነው፡፡ ይሄ ባለመኖሩም ምዝገባ የተከለከለበት አጋጣሚ አልታየም፡፡ ነገር ግን ኤጀንሲው የታክስ

ግዴታቸውን ያልተወጡ ድርጅቶችን ስም ዝርዝር ወደሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን እንደሚያስተላልፍ ታውቋል፡፡

- የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ሠራተኞችን በሚመለከት የገቢ ግብር ለመክፈሉ ማስረጃ እንዲያቀርቡ መጠየቁም ቢሆን double taxationንን የሚከላከል ስለሆነ ለግለሰቦቹም ጥቅም ነው፡፡
- Funding ኤጀንሲዎችን በተመለከተ ሕጉ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር ስለሌለ ኤጀንሲው ጉዳዩን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ እንደሚያወጣ ይጠበቃል፡፡
- በክልል ተመዝግበው የነበሩና የገቢ ምንጫቸውን ግን ከውጭ የሚያገኙ ድርጅቶች በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት ወደ ኤጀንሲው በመቅረብ መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የተዘጋጀው የመመዝገቢያ ቅጽ እነዚህን አካላት ስለማይመለከት ኤጀንሲው የተለየ ቅጽ እንደሚያዘጋጅ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- የበጐ አድራጐት ማህበራት የበጐ አድራጐት ሥራንና የማህበር ሥራዎችን አንድነት ቀላቅሎ መስራት አይቻልም የሚል አቋም ኤጀንሲው እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡
- የኢትዮጵያ ነዋሪዎችና ኢትዮጵያዊ ማህበራትና ድርጅቶች አንድ ላይ ሆነው ጥምረት መመስረትን የሚከለክል ግልጽ ድንጋጌ በሕጉ ውስጥ ባይኖርም ካለው ግንዛቤ ይህ አይነቱ ጥምረት መመስረት እንደማይፈቀድ ኤጀንሲው በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጿል፡፡ ለዚህም የተሰጠው ምክንያት የሁለቱ አካላት ሕብረት ቢመሠረት የኢትዮጵያ ነዋሪ ድርጅቶች ከውጭ የሚያገኙትን ገቢ በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ ማህበራት ወይም ድርጅቶች በማስተላለፍ በአዋጁ ከውጪ ምንጭ ገንዘብ ማግኘትን በተመለከተ የተሰጠውን ክልከላ የሚያስቀር ስለሚሆን የአዋጁን ተፈጻሚነት ይሸረሽራል የሚል ነው፡፡
- የጥምረቶች ምዝገባ በኤጀንሲው አልተጀመረም በቅርቡ ደንብ እንደሚወጣለት ይጠበቃል፡፡
- በአዋጁ አንቀጽ 3 ላይ የውጭ ድርጅቶች የሁለትዮሽ ስምምነት የሚያደርጉበትን ስርዓት በተመለከተ ቢሆንም ይህ ስርዓት ገና አልተዘረጋም፡፡ የፌደራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ከውጪ የሚገኝ የልማት እርዳታን የማስተባበር mandate ስላለው ይህን ሚና ይወስዳል ተብሎ ይገመታል፡፡
- በአዋጁ አንቀጽ 2 (15) ከውጭ ምንጭ የሚገኝ ገቢ ማንኛውም ከውጭ አገር መንግስት ኤጀንሲ ወይም ካምፓኒ፣ አለም ዓቀፍ ኤጀንሲ ወይም በውጭ አገር ካለ ሰው የሚገኝ ገቢን የሚያጠቃልል ሲሆን እንደ የተባበሩት መንግስታት ያሉትን ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ አገሮች አባላት የሆኑበት ተቋም፣ የአውሮፖ ህብረት --- ወዘተ የመሳሰሉት ከዚህ ምድብ ውስጥ ይወድቃሉ አይወድቁም ለሚለው መልስ አልተገኘለትም፡፡
- ስለ ግብር ቅነሳ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1999 አንቀጽ 291(7) እንደተደነገገው ለግብረሰናይ ተልእኮ የሚደረጉ ስጦታዎች ለንግድ ድርጅቶች እንደ ወጪ አየቆጠሩም፡፡ ሆኖም ችሮታዎቹ ወይንም ስጦታዎቹ እንደወጪ የሚቆጠሩባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነሱም በደንብ ቁጥር 78/1995 ተዘርዝረዋል፡፡

## V. ስለአቤቱታና ይግባኝ

በአዋጁ አንቀጽ 104 (3) እንደተቀመጠው በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ የማቅረብ መብት የተሰጠው ለኢትዮጵያዊ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ነዋሪዎችና የውጪ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች የኤጀንሲውና የቦርዱ ውሣኔ ላይ ቅሬታ ቢኖራቸው ይግባኝ መጠየቅ አይችሉም፡፡ የቅሬታ ሰሚ ቦርዱ ገና አልተቋቋመም፡፡ በምዝገባ ጊዜ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት እንዲችል (ቦርዱ መቋቋም ነበረበት የሚል የጽሁፍ አቅራቢው እምነት ተገልጿል፡፡)

አሁን ባለው አሰራር አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ከበጐ አድራጐት ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችን የሚፈራረም ሲሆን ከአዲሱ አዋጅ አኳያ ይህንን ስምምነት መፈራረም ያለባቸው የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ወይም ኤጀንሲው ራሱ መሆን ስለሚገባው ይህንን የሚመለከት አሰራር ይዘረጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## VI. ከተሳታፊዎች የተነሱ ጥያቄዎች

1. የመሸጋገሪያ ጊዜው grace period ነው?
2. በአዋጁ መሠረት የፕሮጀክት ሠራተኞች ደሞዝ እንደ አስተዳደራዊ ወጪ ይቆጠራል?
3. ለጥምረቶች ዳግም ምዝገባ የአባላት ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የተወሰነበት ቃለጉባኤ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡ የተመዘገቡት ድርጅቶች ብቻ ነው ያልተመዘገቡትን ይጨምራል?
4. ኔትዎርኮችን በተመለከተ ለምሣሌ CTF /cotonou Task Force/ በ2010 ስራውን የሚያጠቃልል ሲሆን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አለማቀፍ ተቋማትን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ተቋማት እንድ ላይ ኔትዎርክ መመስረት ይችላሉ?
5. ታክስን በሚመለከት ለምሣሌ ከፕሮጀክት ጋር በተያያዘ መኪና ቢገዛ ታክስ ባይከፍልም ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ለመንግስት አካል ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለቢሮ አገልግሎት ከሆነ ታክስ ይከፈላል ይህ አሰራር ከአዋጁ አንጻር እንዴት ይታያል?
6. ስለ income generation ማብራሪያ ቢሰጥ?
7. የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የሆኑ ድርጅቶች ጥምረት በአዋጁ የተከለከለ አይመስልም፡፡ ስለሆነም ይህ ተፈቅዶ የገቢ አጠቃቀምን በተመለከተ በመመሪያ ቢቀመጥ ችግሩን ሊያቃልል አይችልም ወይ?
8. ድርጅቶች እስከ የካቲት ድረስ የጀመሩት ሥራ እንዲቀጥሉ እና ከዚያ በኂላ አዋጁ ተፈጻሚ እንደሚሆን ነበር ያለው አስተሳሰብ ኤጀንሲው ይህን እንዴት ያየዋል?

## VII. ከተሳታፊዎች ለተነሱ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች

አቶ አታክልቲ ግደይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ /አስተያየት ሰጥተዋል።

- በአዋጁ አንቀጽ 57 (6) እና አንቀጽ 69 ላይ የተጠቀሰው የአምስት ክልሎች ውክልና አዲስ አበባ እና ድሬዳዋን የማይጨምርበትን ምክንያት ሲያብራሩ፡-

  የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርዓት የተገነባው በ9 ክልሎች ነው አንድ ፌደራላዊ ተቋም ለመመስረት ቢያንስ የክልሎቹ simple majority 50% ይሁንታ ያስፈልጋል። በዚህ ስሌት መሠረት ቢያንስ የ5 ክልሎች ማለት ነው። ይህን መሠረት በማድረግ ነው አዋጁ የተቀረጸው። ድሬዳዋና አዲስ አበባ ቢጨመሩ ኖሮ 11 ክሎች ስለሚሆኑ ከላይ በተጠቀሰው ስሌት 6 ክልሎች በተባለ ነበር። ስለሆነም ድሬዳዋና አዲስ አበባ እንደ ክልል ሆነው ቁጥር ውስጥ ሊገቡ አይችሉም።

  በተጨማሪም እንደሚታወቀው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በማንኛውም የአገሪቱ ክልል ተዘዋውሮ የመስራት መብት ስላለው ከግምት ውስጥ የሚገባው በክልሉ ነዋሪነቱ ነው። ስያሜውም የፌደራል ባህሪ የሚያንጸባርቀው የኢትዮጵያ … ቢል ሲሆን ለምሣሌ ስያሜው ኢትዮጵያ ትቅደም--- ድርጅት ከሆነ በኢትዮጵያ ደረጃ መቋቋሙን ስለማያመለክት የግድ የክልሎችን ይሁንታ እንዲያገኝ አይጠበቅበትም።

- ጽሑፍ አቅራቢው ምዝገባ ሲከለከል አንቀጽ ጠቅሶ መሆን አለበት ያሉት በመርህ ደረጃ ተቀባይነት አለው። በአዋጁ አንቀጽ 69 ላይ የተዘረዘሩት ምዝገባን የሚያስከለክሉ ምክንያቶች ሲያጋጥሙ እና ኤጀንሲው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ ሲደርስ አንቀጹን በመጥቀስ ሙሳኔውን ማሳወቅ ይኖርበታል። ይህ ቅሬታን ለማቅረብም የሚያመች ይሆናል። ነገር ግን እስከአሁን በኤጀንሲው የነበሩት አሰራሮች ተመዝጋቢዎች የጐደሉትን ነገሮች እንዲያውቁ እና እንዲያሟሉ የማድረግ ሥራ ነበር።

  ሲጠበቅ የነበረው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 168/2002 ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል።

  Consortium እንዴት እንደሚመዘገብ የሚወጣው ረቂቅ መመሪያ ከ2 ሣምንታት በኋላ ለውይይት ይቀርባል። ከጥር ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል በዚህ አይነት የሚመዘገቡ Consortiums ከ 15 አይበልጥም ስለሆነም በአጭር ጊዜ ውስጥ ምዝገባውን ለማካሄድ ይቻላል።

- በዳግም ምዝገባ ጊዜ ድርጅቶቹ የሚገኙበትን የንብረት እና የገንዘብ ሁኔታ ማወቅ የኤጀንሲው ግዴታ ነው።
- ታክስ የመክፈል ግዴታ ጽሁፍ አቅራቢው እንደጠቀሰው በሌላ የታክስ ሕግ መሠረትም የተጣለው ግዴታ መከበር አለበት። ይህን ግዴታ ያልፈጸሙትን በሚመለከት የተገኘውን

መረጃ ወደሚመለከተው የመንግስት አካል ከማስተላለፍ ውጪ እስከ አሁን በዚህ ምክንያት እንዳይመዘገቡ አልተደረገም።

- በአዋጁ አንቀጽ 3(2) ስለሁለትዮሽ ስምምነት የተጠቀሰውን በተመለከተ መመሪያ መውጣት አለበት። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይህን ሚና ይወስዳል የተባለው የጽሑፍ አቅራቢው የግል ግምት ነው። መንግስት የራሱ ኮሚቴ አውጥቶ እየሰራበት ነው፤ መመሪያም ያወጣል።
- በየክልሉ የተመዘገቡት ከ 10 በታች ናቸው።። ሰፊ ቁጥር ያለው አዲስ አበባ ነው በአንድ ክልል ውስጥ የሚሠራ ከ 90 % በላይ የገቢው ምንጭ ከውጪ ከሆነ ኤጀንሲው ጋር ቀርቦ መመዝገብ ይገባዋል። ገቢውን ከአንድ ክልል በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደርና በዛው ክልል የሚሰራ ከሆነ ብቻ በክልሉ ይመዘገባል።
- በአዋጁ አንቀጽ 15 ላይ እንደተገለጸው የጋራ አላማን ለማስፈጸም ሲባል ጥምረት መመስረት ይቻላል። የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ነዋሪ በሚመለከት የተደረጉት ገደቦች ዓላማ አንዱ በሌላው አንደበት እንዳይናገር ከውጪ በተገኘ ፈንድ ያልተፈቀደለት ተቋም እንዳይጠቀም ነው።
- የቅሬታ ሰሚ ቦርድ ለማቋቋም በመንግስት በኩል 5 ሰዎች ለቦርድ አባልነት ተዘጋጅተዋል። ከሲቪል ማበራት 2 ሰዎችን ለመጨመር የጋራ የሲቪል ማህበራት ፎረም ባለመኖሩም ምክንያት አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥራል። በሚቀጥሉት 2-3 ሣምንታት ቦርዱ እንደሚቋቋም ይታሰባል።
- የድርጅቶች ስያሜን በተመለከተ ከተፈለገ የአማርኛውን ስያሜ በእንግሊዝኛም ተተርጉሞ ቢቀርብ ይቻላል። ነገር ግን በአሰራር ግዴታ አይደለም።
- የመሸጋገሪያው አንቀጽ አላማ የሲቪል ማህበረሰቡ በሙሉ ባለው “grace period” ተዘጋጅቶ እንዲመዘገብ ለማድረግ ነው። ሕጉ ከመውጣቱ በፊት የታቀዱ ስራዎች ሳይደናቀፉ እንዲጠናቀቁ እድል ለመስጠት የተሰጠ ጊዜ ቢሆንም ሕጉ ሥራ ላይ የሚውለው በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው።
- 30/70ን በሚመለከት ኤጀንሲው ዝርዝር መመሪያ እያወጣ ነው። እስከአሁን ያልወጣበትም ምክንያት ሕጉ አስፈላጊ (relevant) የሚሆነው ሥራ ውስጥ ከተገባ በኋላ ነው በሚል አስተሳሰብ ነው። የዓላማ ማስፈጸሚያ እና የአስተዳደር ወጪዎች የትኞቹ እንደሆኑ የስራ ባሕሪውን፣ ወጪዎቹ ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር ያላቸውን ዝምድና --- ከግምት ውስጥ በማስገባት (on case by case basis) የሚታይ ይሆናል።
- ጥምረቶችን ለመመዝገብ የተመዘገቡት የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ቃለጉባኤ ነው የሚያስፈልገው፣ ያልተመዘገቡትን አይጨምርም
- ቀደም ሲል በፍትህ ሚ/ር የተቀመጡትን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን መዝገቦች ለማየት ተሞክሮ ነበር። ከተገኙት 3,822 መዝገቦች ውስጥ ከ1999 በፊት የታደሱት እንደ “inactive” ተወስደው 1,179 ግንኙነት ያቋረጡ ሲሆኑ የተቀሩት 1,918 “active” እንደሆኑ ተወስዷል። እስከአሁን 1100 ድርጅቶች የተመዘገቡ ሲሆን ካሁን በኋላ ለምዝገባ የሚቀርቡት ከ500 በላይ እንደማይሆኑ ነው።

- የcotonou ኘሮጀክትን በሚመለከት የcoalition ጉዳይ ቀስ ብሎ በዝርዝር የሚታይ ነው፡፡ የnetworks ምዝገባን በተመለከተ መመሪያ ይወጣል፡፡
- የጥምረቶችን አመሰራረት በተመለከተ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች እና የኢትዮጵያ የሆኑ ድርጅቶች አንድ ላይ ጥምረት እንዲመሠርቱ ተፈቅዶ ከውጪ በተገኘው ገንዘብ የኢትዮጵያ ሆነው የተመዘገቡት እንዳይጠቀሙበት በመመሪያ ማስቀመጥ አይሻልም ወይ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ ጥምረቱ በአዋጁ አንቀጽ 15 እና 55 መሠረት ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ የትኛው ገንዘብ ለየትኛው አላማ ዋለ ብሎ ለመለየት እና ለመቆጣጠር ይመቻል ወይ? መርሁስ ይፈቅዳል? የተከለከለ እና ያልተከለከለን ማገናኘት ነገሩን ያወሳስበዋል፡፡
- በክልል የተመዘገቡትን ማህበራትን በምን መልክ ነው ጥምረቱ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉት ለሚለውም ከ2-3 ሳምንታት በኋላ ኤጀንሲው መረጃ ይሰጣል፡፡
- የሲቪል ማህበራት task force ለቦርዱ አባልነት ሁለት ሰው ለመምረጥ ሊያመቻች ይችላል፡፡ ድርጅቶች ህጉ እንዲሰሩ በፈቀደበት ሥራዎች ላይ advocacy ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡
- በክልሎች የተፈቀደ እና ያልተፈቀደን የስራ ዘርፍ መለየትን በተመለከተ የግንዛቤ ችግር ካለ በሂደት ችግሩን ለማቃለል ጥረት ይደረጋል፡፡